የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ ሙስሊምን ማማትና ክብሩን መግፈፍ ክልክልነቱን ትምህርት ይሰጡናል። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ [ወደ ሰማይ ባረግኩበት ሌሊት፤ ከነሃስ የሆነ ረጃጅም ጥፍር ያላቸው፤ ፊቶቻቸውንና ደረቶቻቸውን የሚቧጭሩ በሆኑ ሰዎች ዘንድ አለፍኩ። ጂብሪል ሆይ! እነኚህ እነ ማን ናቸው? አልኩት። ጂብሪልም፦ "እነኚህ... የሰውን ሥጋ በሓሜት የሚበሉና በመብቶቻቸው ጣልቃ የሚገቡ ናቸው።" አለ።]

የኢስራእንና የሚዕራጅን ተዓምር፤ በትኩረት የሚያስተውል ሰው፤ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ግሳጼዎችና ማስረጃዎችን ያገኛል። ከነዚህም፤... የአሏህ ባሪያ የሆነ ችግር ሲገጥመው ወይም ጭንቀትና መከራ ሲደራረብበት፤ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዳደረጉት፤ የሩቅ እውቀቶችን አዋቂ ወደ ሆነው (አምላኩ) የድረስልኝ ጥሪውን ያቀርባል። አላህም የመልዕክተኛውን የእርዳታ ጥሪ ሰምቶ ረድቷቸዋል። ችግሮቻቸውንና መከራዎቻቸውን አግርቶላቸዋል።

ምንጭ፦ ከእስልምና ጉዳዮች ባለ ሥልጣን ድረ ገጽ የተወሰደ


P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E

www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae

800 555 اتصل على JUST CALL


دار زايد للثقافة الإسلامية

Zayed House For Islamic Culture

# الإسراء والمعراج

## اللغة الأمهرية

# ኢስራእ እና ሚዕራጅ

# ኢስራእ (የመልዕክተኛው ከመካ ወደ ፍልስጤም የሌሊት ጉዞ) እና ሚዕራጅ (ወደ ሰማይ እርገት)

የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ ከታላላቅ ተዓምራቶች አንድ ነው። ታሪኩን በማወቅ ትምህርታዊ ግንዛቤዎችንና ምክሮችን ለመውሰድ፤ የታሪኩን ክስተት በትኩረትና በማስተንተን ልንረዳው የግድ ይለናል። አላህ እንዲህ ብሏል፡- (ክብር ለዚያ... ባሪያውን [ሙሐመድን] ከተከበረው [የሓረም] መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደባረክነው ሩቁ [የአል አቅሷ] መስጊድ በሌሊት ለወሰደው [አምላክ] ይሁን። ተዓምራታችንን ልናሳየው [ይህን አደረግን]። እነሆ እርሱ [አላህ] ሰሚም ተመልካችም ነው።) [ቅዱስ ቁርኣን ምዕ፡- 17 ቁ. 1]

የኢስራእና የሚዕራጅ ጉዞ፤ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በመካና በጧኢፍ ውስጥ፤ ሰዎችን ወደ ኢስላም ለመጣራት፤ ላደረጉት ጥረት የደረሰባቸውን አደጋዎች በሙሉ በትዕግስት ዋጥ አድርገው ለማሳለፋቸው፣ የአጎታቸው (አቡ ጧሊብ) እና የባለቤታቸው (ኸዲይጃ) ሞት ሃዘናቸውንም በማጽናናት፣ ውስጣቸውን ለማበረታታት እና ደረጃቸውን ለማላቅ በማሰብ፤ የተደረገ አምላካዊ የክብር ሽልማት ነው።

# የኢስራእ (የመልዕክተኛው ከመካ ወደ ፍልስጤም የሌሊት ጉዞ) እና የሚዕራጅ (ወደ ሰማይ እርገት) ታሪክ

የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ያላቸውን የላቀ ክብርና፣ በነቢያቶች መካከል የተሰጣቸውን ለየት ያለ ደረጃ ያመላክታሉ። በቤተ መቅደስ ውስጥም፤ የነቢያቶች (ኢማም) አሰጋጅ ሆነው አሰግደዋቸው ነበር። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- [ከዚያም ቤተ መቅደስ ገባሁ። ነቢያቶችን በሙሉ ሰበሰበልኝ። ጂብሪልም እኔን ወደፊት አስቀደመኝ። ከዚያም አሰገድኳቸው። ከዚያም ወደ ሰማይ ይዞኝ አረገ።]

የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ የተለያዩ ነቢያቶችን የሚከተሉ ህብረተሰቦችን፤ ወደ አንድነት፣ አብሮ በመኗኗር፣ ለመቻቻል፣ ለመዋደድና ለሰላም ጥሪውን ያቀርብላቸውል። ይህ የሆነበት ምክንያት ነቢያቶች አንድ መለኮታዊ መልዕክትን ለማድረስ የተላኩ ወንድማማቾች ስለሆኑ ነው። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- [ነቢያቶች ወንድማማቾች ናቸው። እናቶቻቸው የተለያዩ ናቸው። ሐይማኖታቸው ግን አንድ ነው።]



የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ ግዴታ ያልሆኑ ሰላቶች ያላቸውን ደረጃም ያመላክታሉ። ኢብን ዓባስ፤ አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸው፤ እንዲህ አለ፡- "ነቢዩ መሐመድ ወደ አል አቅሷ በተጓዙበትና ወደ ሰማይ ባረጉበት ሌሊት፤ ጀነት ገብተው የሆነ አይነት ድምጽ ሰሙ። እንዲህም ጠየቁ፡- [ጂብሪል ሆይ! ይህ ድምጽ ምንድን ነው?] ጂብሪልም፡- [ይህ አዛን (ለሰላት ጥሪ የሚያደርገው) ቢላል ነው።] አላቸው። መልዕክተኛውም እንዲህ አሉ፡- [ቢላል ሆይ! በእስልምና ውስጥ፤ ባንተ ዘንድ ጥቅም ያለውና ተወዳጅ የሆነ ሥራህን ንገረኝ። እኔ በጀነት ውስጥ ያንተን የጫማ ኮቴ ድምጽ ግልጽ በሆነ መልኩ ሰምቼያለሁ?!] ቢላልም እንዲህ አለ፡- "በኔ ዘንድ እስልምና ውስጥ ጥቅም ያለውና ተወዳጅ የሆነ ሥራ የሠራሁት፤ በሌሊት ወይም በቀን የሆነ አይነት ንጽህና አድርጌ ከጨረስኩ በኋላ፤ አላህ የፈቀደልኝን ያክል ከመስገድ ወደኋላ አልልም ነበር።"

የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ የመስጊድን ክብርና ደረጃም ያመላክታሉ። ይህ ታላቅ ጉዞ ጅምሩ ከተከበረው መስጊድ ነው። ይህም መስጊዶች በህይወታችን ውስጥ ያላቸውን የላቀ ክብር ያመላክተናል። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ይህን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡- [እነዚህ መስጊዶች (አገልግሎታቸው) ክብሩ የላቀውን አላህን ለማወደስና ለማውሳት፣ እንዲሁም ለስግደትና ቁርኣንን ለማንበብም ነው።]

የኢስራእና የሚዕራጅ መታሰቢያ፤ አላህን ማውሳትና ማወደስ ያለውን የላቀ ክብርም ያመላክታሉ። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- [በሌሊቱ ጉዞዬ ውስጥ፤ ነቢዩ ኢብራሂምን አገኘሁት። እርሱም፡- [ሙሐመድ ሆይ! ለህዝቦችህ ሰላምታዬን አድርስልኝ። ይህንንም ንገራቸው... ጀነት መልካምና ውብ እንደሆነች፣ ውሃዋ ጣፋጭ እንደሆነ፣ ዛፍ የሌለባት ሰጥ ረጭ ያለች ምድር ናት። ይህችን ምድረ-በዳ ምድር ማልሚያው (ሰብሃነላህ... [አላህ ጥራት ተገባው] አልሓምዱሊላህ... [ምስጋና ለአላህ ይሁን] ላኢላሃ ኢለላህ.... [ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም!] አላሁ አክበር... [አላህ ታላቅ ነው]።) የሚሏቸው የውዳሴ ቃላቶች ናቸው።]